# “ካልቀለጠው ሻማ” ምን እንማር?

**ዘአማን በላይ** 08-23-17

አምስት ዓመታት ረጅም ባይሆኑም፤ አጭር ግን አይደሉም። ብዙ የሰራንባቸው፣ ተግዳሮቶችን ተጋፍጠን ያለፍንባቸው እንዲሁም በትዝታ ባህር ውስጥ ሆነን በርካታ ትውስታዎችን የዘከርንባቸው ዓመታት ናቸው። ታዲያ በእነዚህ ዓመታት ሁሌም ከአዕምሯችን የትውስታ ማህደር ውስጥ የማይጠፉ አንድ አፍሪካዊ ኮከብ አሉ—ታላቁ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ አስረስ።

አቶ መለስና ዘመን ተሻጋሪ ራዕያቸው፣ በሳል አስተምህሮቻቸውና ሁለንተናዊ ስብዕናቸው ሁሌም ከእኛ ጋር አብረውን አሉ። እኛነታችንን በሰላም፣ በልማትና በዴሞክራሲ ለማፍካት እንደ ጥላ ይከተሉናል። ታላቁ መሪ ያልቀለጠ ሻማ ናቸው። እርሳቸውና ድርጅታቸው የለኮሱት ድህነትን የማጥፋት ችቦን እየተቀባበልን ዛሬ አምስተኛው ሙት ዓመታቸው ላይ ደርሰናል። እኔም እንደ ሀገራችን ባህል “ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑራት” ብያለሁ።

ዛሬ አምስተኛ ሙት ዓመታቸው ላይ ሆነን መለስን ስናስታውሳቸው፤ ስለ ሁለንተናዊ አስተምህሮቻቸውና ስለ ስብዕናቸው በመጠኑም ቢሆን ማውሳት ቢያንስ እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም። እግረ መንገዱንም በየደረጃው የሚገኝ አዲሱ አመራር ጥልቅ ባህርና ህልቆ መሳፍርት የሆኑትን የመለስን አስተምህሮዎች እንዲሁም ታላቁ መሪ የለኮሱትን የህዳሴ ችቦ ይበልጥ አቀጣጥሎ የአገራችንን ህዳሴ እውን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ለመጠቆም እሞክራለሁ።

አቶ መለስ ከእውቀትና እውነት ጋር ተቀምመው ለዚህ ትውልድ የተሰጡ ገፀ-በረከት ናቸው። ከዘመናችን ብርሃን ሰጪ ከዋክብት አንዱም ጭምር። ለህዝብ ኖረው ለህዝብ የሞቱት አቶ መለስ ስለ ሰላም ባክነዋል። ለአንድነታችንና ለሰላማችን ሌት ተቀን ማስነዋል። እንደ ሻማ እየቀለጡና እየነደዱ ብርሃን ሰጥተውናል። እርሳቸው ሳይኖሩ፣ እኛን አኑረውናል።

ህልቆ መሳፍርት የሌለው ሰው እንደሚመሰክረው የአቶ መለስ ስብዕና የረቀቀ ቢሆንም፤ እኛ የምናውቀው ግን ኢምንቱን ብቻ ነው—ለዚያውም ካወቅነው ማለቴ ነው። ስብዕናቸው ከሰማይ አድማስ የራቀ እንዲሁም ከውቅያኖስ የጠለቀ ጠቢበኛ፣ ባለ ራዕይ ብሎም “የነገ ሰው” እንድንሆን ፊት ለፊት እየቀደሙ ትክክለኛውን መንገድ ያሳዩን ብርቅዬ የህዝብ ልጅ ናቸው። ያም ሆኖ የታላቁ መሪ ራዕይ፣ ተስፋና ህልማቸው በእጃችን ላይ ስላሉ እነሱን እያስቀጠልን፣ በእነርሱው እየፈካንና እየደመቅን እውን መሆኑ የማይቀረውን ህዳሴያችንን አሻግረን እንለመከታለን።

ቀደም ሲል እንዳልኩት የመለስን የረቀቀ ስብዕና እና አስተምህሮቶችን ሁሉንም መጥቀስ ባይቻልም፤ በፀረ-ድህነት ትግልና በዲፕሎማሲ ረገድ ስለነበራቸው አቋም እንዲሁም የእርሳቸው “የእጅ ስራ” ስለሆነውና በርካታ አገራት “በሞዴልነት” ስለሚከተሉት የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ብሎም ስለ ሰሞነኛው ፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት እሳቤያቸው የተወሰኑ ጉዳዩችን ማንሳት በየደረጃው የሚገኘው አዲሱ አመራር እነዚህን ጥልቅ እሳቤዎች “መለስ” ብሎ እንዲያያቸው ያግዘዋል ብዬ አምናለሁ።

አቶ መለስና ድርጅታቸው የተረከቧት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መዝገበ-ቃላት ላይ ሳይቀር የድህነት ምሳሌ ተደርጋ የምትጠቀስ ነበረች። ይሁንና የሀገሪቱን ሁለንተናዊ መልክ ሁለት አስርት ባልሞሉ ዓመታት ውስጥ ለመቀየር በተደረገው ጥረት ስሟ አንገት ከሚያስደፋው ስያሜ እንዲፋቅ ተደርጓል። እንዲያውም ታላቁ መሪያችንና

ድርጅታቸው ፖሊሲያቸውንና ስትራቴጂያቸውን ምርኩዝ በማድረግ ባከናወኑት ህዝቡን ከጫፍ እስከ ጫፍ ያነቃነቀ ልማታዊ ስራ ሀገራችን በዓለም ላይ ፈጣንና ተከታታይ ልማትን ከሚያስመዘግቡ ጥቂት ሀገሮች ተርታ ውስጥ እንድትሰለፍ አድርገዋል። በዚህም አቶ መለስ በስልጣን ላይ በነበሩባቸው ዓመታት የተጀመረው የሀገራችን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት እያስመዘገበ ዛሬም ቀጥሏል።

ታላቁ መሪ በህይወት በነበሩበት ወቅት "ከድህነት በላይ ክብርን የሚነካ ጠላት የለም፤ የድህነት ተራራ የሚናደው በእውቀት ጥይት ነው" ብለው ነበር። ይህን የእውቀት ጥይት በስራ ላይ በማዋል ትክክለኛ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለሀገራችን ከማበርከት ባሻገር በየደረጃው ያሉ አመራሮች "በእውቀቱ" እንዲደረጁ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በማከናወን ረገድ ጉልህ ሚና ነበራቸው።

በሀገራችን ውስጥ ይታዩ የነበሩ የተለያዩ ተግዳሮቶችን ብልህነትና አስተዋይነት በተሞላበት መልኩ ሲያከናውኑ የነበሩ ናቸው። "መንግስት መታገስ አለበት። መልፈስፈስ ግን የለበትም" የሚል ፅኑ አቋም በማራመድ፣ ነገሮችን አስቀድሞ በመተንተንና ከተከሰቱም እንደ አመጣጣቸው የመፍታትት ክሂልን ያዳበሩ መሪ ናቸው።

ታላቁ መሪ በዲፕሎማሲው ረገድም ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። አቶ መለስ አሸባሪነትንና አክራሪነትን በቀጣናው እንዳያቆጠቁጥና ምስራቅ አፍሪካ ከጽንፈኞች ስጋት ነፃ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉ መሪ ናቸው። ሶማሊያ መንግስት አልባ በነበረችው ወቅት በምስራቅ አፍሪካ ሰማይ ላይ እንዲያንዣብብ ያደረገውን የጦርነት ደመና ብስለት በተሞላው ዘዴ አስወግደዋል። በወቅቱ የኢጋድ አባል ሀገራትንና አፍሪካ ህብረትን ከጎናቸው በማሰለፍ የሶማሊያ አክራሪ ፅንፈኞች አከርካሪያቸው እንዲሰበር ለማድረግ የቻሉ የሰላም መሪ ናቸው። በዚህም ወታደራዊ ስትራቴጂና ታክቲክን በመቀመርና የሀገራቸውን ሰራዊት ብቃት ለዓለም በማሳየት አስተማማኝ ወታደራዊ ዲፕሎማሲን መገንባት ችለዋል።

ሶማሊያ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ያለው አሸባሪው አልሸባብ ለቀጣናው ያለውን አስጊነት አስቀድመው በመገንዘብ የምስራቅ አፍሪካን የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመሆን ሀገራት ወደዚያች ሀገር ሰራዊታቸውን እንዲልኩ ባከናወኑት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ ሶማሊያ አሁን ለምትገኝበት አንፃራዊ ሰላም ወሳኝ ተግባር ፈፅመዋል። ከሁሉም ጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለመፍጠር ደፋ ቀና ይሉ የነበሩት እኚህ ታላቅ የአፍሪካ ልጅ፤ ለየትኛውም ወገን የማይወግን የዲፕሎማሲ አካሄዳቸውን በመጠቀም ደቡብና ሰሜን ሱዳን ችግራቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ አስችለዋል።

በጥቅሉ የአቶ መለስ ራዕይ ብርሃናዊ ውጋገኑ ከኢትዮጵያም አልፎ በምስራቅ አፍሪካ ሰማይ ላይ ደምቆና ፈክቶ ታይቷል። የቀጣናው ሀገራት ሰላማዊ ድባብ እንዲሰፍንባቸው እንዲሁም በምጣኔ-ሃብት እንዲተሳሰሩ ሰንቀውት የነበረው ህያው ልማታዊ ሃሳብ ከተምሳሌታዊ አፍሪካዊ ተግባራቸው ተቆርሶ የሚታይ ነው።

መለስ በምስራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት እንዲጎለብትና እንዲረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ፤ አፍሪካ የልማት እንጂ የጦርነት አውድማ እንዳትሆን ሳይታክቱ ሰርተዋል። ለዘመናት የግጭትና ያለመግባበት አብነት ተመስሎ የሚታየውን የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ወደ አንፃራዊ ሰላም በመመለስ፤ ክፍለ-አህጉሩ በልማት የትስስር ድር እንዲያያዝ ለማድረግ የጣሩ ብርቅዬ የአፍሪካ ልጅ ናቸው።

ምን ይህ ብቻ። አቶ መለስ ከምስራቅ አፍሪካ ባለፈም የአህጉሪቱን ጥቅሞች ለማስከበር ሌት ተቀን ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ የአህጉሪቱ ታላቅ ባለውለታ ናቸው። አህጉሪቱ ከሌሎች ሀገራት ጋር አንዳች ዓይነት ውይይት የምታካሂድ

ከሆነና በቦታው እኚህ የአፍሪካ ልሳን ካሉ፤ ያለ አንዳች ጥርጥር የውይይቱ ውጤት ወደ አፍሪካ ማዘንበሉ አይቀሬ ይሆናል። ምናልባትም ውይይቱ አስቸጋሪ ከሆነ፤ ፍፃሜው እኩል በእኩል በሆነ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ሸንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ። ብቻ አፍሪካ በጥቅሞቿ ዙሪያ በምታካሂደው ማንኛውም ድርድር ወቅት የታላቁ መሪ መገኘት፤ ውይይቱ በአህጉራችን የበላይነት እንዲፈፀም ያደርጋል። ያኔ አፍሪካም ሐሴትንና ፍሰሐን ታደርጋለች። ታላቁ መሪ እንዲህ ናቸው።

አቶ መለስ እያንዳንዱን አስተሳሰባቸውን ከማራመድ ባሻገር ራዕያቸውን በወረቀት ላይ ከትበው ለመጪው ትውልድ ከማስተላለፍ ወደ ኋላ ያሉበት ወቅት የለም። ከዚህ አኳያ እርሳቸው የጀመሩት የአረንጓዴ ልማት ተጠቃሽ ነው። በተለይም በየዓመቱ በአማካይ በሁለት ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይጨምራል ተብሎ በሚጠበቀው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ "አፍሪካ ዋነኛዋ ተጎጂ ናት" በማለት የምዕራቡ ዓለም በኢንዱስትሪ ሳቢያ ለፈጠረው የካርቦን ልቀት ለአህጉሪቱ ካሳ እንዲከፍል በመጠየቅ ከአፍሪካ ህዝቦች ባሻገር ከራሳቸው ካደጉት ሀገራት ጭምር አንቱታን ለማትረፍ መብቃታቸውን እናስታውሳለን።

መለስ በኪራይ ሰብሳቢነትና በሙስና ላይ የማይናወጥ አቋም የነበራቸው የህዝብ ወገንተኛ መሪ ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት "የኢትዮጵያን ዕድገት አንድም ጋት ወደ ኋላ የሚጎትት የሀገራችን ጠላት ነው" በማለት የኪራይ ሰብሳቢነትንና የሙስናን አስከፊነትና በአገራችን ውስጥ ሊፈጥር ስለሚችለው እንቅፋት ሲገልፁ ነበር። እንዲያውም ይህን ተግባር እንዲፈፅም እንዲቋቋም ያደረጉት የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ተግቶ እንዲሰራ "ኮሚሽኑ ጊዜውን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ እያጠፋ ነው" በማለት ይበልጥ ገፋቶ የኪራይ ሰብሳቢነትን አስተሳሰብና ተግባር በመዋጋት ተቋማዊ ኃላፊነቱን አጠናክሮ እንዲወጣ ሲያሳስቡ ነበር። ይህ እሳቤያቸው ዛሬም ከእኛ ጋር በመሆኑ አቶ መለስ ያልቀለጠ ሻማ ያህል ብርሃናዊ መንገድ ሆነውናል።

በአጠቃላይ ከላይ "ዓባይን በጭልፋ" እንዲሉ በጥቂቱ ለማንሳት የሞከርኳቸው "ያልቀለጠውን ሻማ" አስተምህሮዎችና ተግባሮች በየደረጃው የሚገኝ አመራር ብዙ ቁም ነገሮችን ይማራል ብዬ አስባለሁ። ለህዝብ ራስን አሳልፎ መስጠትን፣ በድህነት ላይ የሚደረግ ትግል በእውቀት ላይ በመመስረት እንጂ በአንድ ሰሞን ሆይ…ሆይታ የሚፈፀም አለመሆኑን፣ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ በዲፕሎማሲው መስክ ተከታይ ሳንሆን ቀዳሚና ተጠቃሽ እንዲሁም የሀገር ብሎም የአህጉርና የዓለም መድን መሆን እንደሚቻል ከእርሳቸው መወሰድ የሚገባቸው ጉልህ ተሞክሮዎች ይመስሉኛል።

አቶ መለስ በአስተምህሮቻቸው "የእኛ የትግል ቅብብሎሽ የአጭር ርቀት የዱላ ቅብብል እንጂ ማራቶን አይደለም" እንዳሉት፤ አዲሱ አመራር ይህ የቅብብሎሽ ትግል እንዳይረዝም በሀገራችን ውስጥ የሚታዩ ወቅታዊ ተግዳሮቶችን ባልተራዘመ ጊዜ ውስጥ በመፍታት የኢትዮጵያን ህዳሴ ቅርብ ማድረግ የሚጠበቅበት ይመስለኛል። ይህን በማድረግም "ባልቀለጠው ሻማ" ብርሃን ይበልጥ እንድንደምቅ፣ ሌሎች የረገጡትን ድንጋይ እንድንረግጥና የደረሱበትን ማማ እንድንጨብጥ ሊያደርገን ይችላል።